

# የመለስ መታሰቢያ ተቋም (Foundation) - ክፍል 3 ከ 3

ግርማ ሞገስ (girmamoges1@gmail.com)

ቅዳሜ ግንቦት 11 ቀን 2005 ዓ.ም. (Thursday, May 18, 2013)

የአቶ መለስን መሞት መንግስት ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ይፋ አደረገ። መንግስት ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. የመለስ ራዕይ እንዲቀጥል የኢትዮጵያ ህዝብ በሃዘን መግለጹን የሚያብራራ እና መታሰቢያ ተቋም የሚመሰረት ህግ አወጀ። የመለስ ዜናዊ መታሰቢያ ተቋም የገቢ ምንጭ የግል ለጋሾች፣ ገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች፣ የኢትዮጵያ መንግስት እና ሌሎች ምንጮች እንደሚሆኑ አዋጁ ጨምሮ አብራራ። መጋቢት 29 ቀን 2005 ዓ.ም. ደግሞ ህውሃት 'የመታሰቢያ ተቋም መስራች ጉባኤ' ተብሎ የሚጠራ ሌላ ድራማ በማዘጋጀት የኢትዮጵያ ህዝብ በአቶ መለስ ራዕይ ፍቅር መጠመዱን እና ይኸን ፍቅሩን በሃዘን መግለጹን የተለያዩ ተናጋሪዎች በጉባኤው እንዲያብራሩ አደረገ። የመታሰቢያ ተቋሙ ግቦች እና ተዛማጅ ጉዳዮችም ተነገሩ። በድርጅታዊ የሚስጢር አሰራር ቀደም ብሎ የተመረጡ የቦርድ አባላት በጉባኤው ላይ አንደ አዲስ ተመረጡ። ወ/ሮ አዜብም ፕሬዘዳንት ተደርጋ ተመረጠች። 'መለስ እንደተሰዋ ሁሉ እኛም እስከምንሰዋ ድረስ  ለመስራት ቃል እንገባለን' የሚል የደርግ አይነት መፈክር በማሰማት ምርጫውን መቀበሏን ገለጸች።  ይኸ ድራማ የታየው በአፍሪካ ኅብረት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ነበር። ይሁንና አዜብ መስፍን በጉባኤው ላይ 'እንደ መለስ እስከምንሰዋ ድረስ እንሰራለን' ስትል 'እስክንሞት ድረስ አምባገነናዊ አገዛዛችን ይቀጥላል' ማለቷ ይመስላል። አምስት ነጥቦች አነሳለሁ።

(1ኛ) መጀመሪያ ስለአቶ መለስ ራዕይ፥

የአቶ መለስ ራዕይ ባለፉት ሃያ አመቶች ውስጥ ኤርትራ እንድትገነጠል አድርጓል። ኢትዮጵያ የባህር በር ጥገኛ በመሆን የኢኮኖሚ፣ የንግድ እና ወታደራዊ ነፃነቷ ደረጃው ዝቅ እንዲል አድርጓል። ከዘመዶቻችን ኤርትራውያን ጋር አለያይቶናል። ኤርትራውያንን በትግሪኛ ተናጋሪ አምባገነን እንዲገዙ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከሚኖርባቸው ከሱማሊያ፣ ከአፋር፣ ከደቡብ እና ከቤንሻንጉል-ጉምዝ አካባቢዎች ፖለቲካዊ መፈናቀል እና መባረር እንዲደርስባቸው አድርጓል። ወንጀል የፈጸሙ ሲከሰሱ እና ሲታሰሩ አናይም። ንብረት የተዘረፈባቸው ካሳ ተከፈላቸው የሚል ዜና የለም። ከተፈናቀለው አማርኛ ተናጋሪ ውስጥ ጥቂቱ ወደ ጉርባፈርዳ እና ቤንሻንጉል-ጉምዝ አካባቢዎች ተመለሰ ቢባልም በፌዴራል እና በክልል ፖለቲከኞች ተገቢው መልሶ የማቋቋም እርዳታ አልተደረገም። በወንጀለኞች ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ አልተወሰደም። በተመለሰው ላይ ወንጀለኞች ተስፋ አስቆራጭ ጫናዎች እንዳይፈጠሩ አልተደረገም። ስለዚህ ወደቀድሞ ቦታቸው ይመለሱ የሚለው የባለስልጣኖች ፕሮፖጋንዳ ማደናገሪያ ወሬ እንጂ እርማት ለማድረግ ከልብ የመነቸ እንዳልሆነ በግልጽ እየታየ ነው። በኢሳት፣ በቪ.ኦ.ኤ.፣ በጀርመን ድምጽ እንደምንሰማው እና በድረ-ገጾች እንደምናነበው ከሆነ 'በቀድሞ አካባቢ ተመልሶ መኖር' የሚለው ጉዳይ 'ብርጭቆ ከነቃ አይሆንም እቃ' የሚለውን አባባል በአእምሮዋችን እየጫረ ነው።

የአቶ መለስ ራዕይ ነገ ሊሆን ስለሚችለው እያሰብን እንድንሰጋም አድርጎናል። በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ የተፈጸመው ፖለቲካዊ፣ ህጋዊ እና ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎች ተገቢውን እርማቶች ካላገኙ ነገ እንደ ጽዋ የሌላ ቁንቋ ተናጋሪዎችን በር በተራ ማንኳኳቱ እንደማይቀር እያሰብን እንድንሰጋ አድርጎናል። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ዲሞክራሳዊ አገር ሆና አታውቅም። ጭቆናዎች ተፈጽመዋል። ሚዛናዊ ያልነበሩ ግንኙነቶች ነበሩ። ህዝቡ ግን እስቲ ይሁን ብሎ አብሮ የመኖር ፈቃደኛነትን እና አንድነትን ገንብቷል። የአቶ መለስ ራዕይ ግን እየተፈታተነው ነው። ህዝቡ የገነባውን አንድነት ጠብቆ ነባር ጭቆናዎችን እና ሚዛናዊ ያልነበሩ ግንኙነቶችን ማስወገድ ይቻላል። የአቶ መለስ ራዕይ ግን ይኺን አኪያሄድ ከጥንት ጀምሮ አይፈቅድም። የዛሬ 40 አመት ግድም በጋራ ትግል አምባገነናዊ ስርዓትን በኢትዮጵያ ማስወገድ ይቻላል ሲባል አቶ መለስ እና ባልደረቦቹ ህውሃቶች አልተቀበሉም ነበር። የአቶ መለስ ራዕይ ዛሬም ያው የጥንቱ ነው። ዛሬም እንደቀድሞዎቹ ሃያ አመቶች የመንግስት ስልጣን የጨበጠው የአቶ መለስ ራዕይ አራማጁ ህውሃት እና ደጋፊዎቹ ናቸው። ስለዚህ የፖለቲካ መፈናቀል እና የዘር ማጽዳት ወንጀል በሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ ሊፈጸም ይችላል የሚለው ስጋታችን ትክክል ነው። የአቶ መለስ ራዕይ ካልተወገደ።

አንባቢ ልብ በል። የመለስ ራዕይ በኢትዮጵያ የፌዴራል እና የክልል ተቋሞች ውስጥ ተሰግስጓል። የመለስ ራዕይ በህገ-መንግስቱም ውስጥ የሚደግፉት አንቀጾች አሉ። ላብራራ። በቅርቡ በኢትዮጵያ መፈናቀል የደረሰባቸው አማረኛ ተናጋሪዎች በህጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት ለኢትዮጵያ የህገ-መንግስት ተርጓሚ ፌዴራል ምክር ቤት አቤቱታ እንዳቀረቡ በየድረ-ገጹ ተነቧል። አቤቱታ መቅረቡ ስህተት አይደለም። ነገር ግን ይኸ የፈዴሬሽን ምክር ቤት የተሞላው በፖለቲከኞች እንጂ ከፖለቲካ ነፃ በሆኑ ሙያተኛ ህግ እና ህገ-መንግስት ተርጓሚ ዳኞች አይደለም። በዚህ ምክር ቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች በመለስ የተመረጡ ስለሆኑ የመለስን ራዕይ የሚጋሩ ናቸው ብንል ስህተት አይሆንም። ሃቁም እሱ ነው። የብሄረሰቦች ቀን ማክበር ትልቁ ስራ ነው የዚህ ምክር ቤት። ስለዚህ የአቶ መለስ ራዕይ የሚቀጥል ከሆነ በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ላይ ፖለቲካ የበላይነቱን እንደጨበጠ ይቀጥላል ማለት ነው። ሌላ ምሳሌ ልጨምር። በየክልሉ የመሬት ባለቤት የክልሉ ብሄረሰብ መሆኑ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት

ተደንግጓል። ስለዚህ በየክልሉ ኢትዮጵያዊነት የሚለው የፖለቲካ ምንነት ብቻውን የክልሉ መሬት ባለቤት አያደርግህም ማለት ነው። የብሄሮች የክልል መሬት ባለቤትነት እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያዊነትም የባለቤትነት መብት ሊያሰጥ እንዲችል የሚያደርግ ህጋዊ እርማት ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ የአቶ መለስ ራዕይ እንዲቀጥል ከተደረገ በክልሎች ውስጥ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች መፈናቀል እና ዘር የማጥራት ወንጀል ሊቀጥል ይችላል ማለት ነው። ይኽ አደጋ የዛሬ አደጋ ነው። አደጋው በግልጽ የሚታይ አደጋ ነው። አንባቢ ልብ ሊል ይገባል።

የመፈናቀል ዜናው፣ ጭቅጭቁ፣ እሮሮው፣ ለቅሶው ይቀጥላል የአቶ መለስ ራዕይ እስካልተወገደ ድረስ። እስከመቼስ ድረስ ስለመፈናቀል ማውራት ይቻላል? ስለዚህ አንድ ደረጃ ሲደረስ መታከት እና መሰላቸት የተባሉት ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውይይት ውስጥ እግራቸውን ሊያስገቡ ይችላሉ። መታከት እና መሰላቸት በአንዳንድ መንፈሰ-ደካማ ሰዎች አዕምር ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይኽ አደጋ የትናንት ሳይሆን የዛሬ አደጋ ነው። አደጋው በግልጽ የሚታይ ነው። አንባቢ ልብ ሊል ይገባል።

(2ኛ) የኢትዮጵያ ህዝብ የአቶ መለስ ራዕይ እንዲቀጥል ጠይቋል ስለሚባለው ጉዳይ ጥቂት ልበል፥

ከመቼ ወዲህ ሃዘን መድረስ ህዝበ-ውሳኔ (Referendum) ማድረግ እንደሆነ ባይነግሩንም የተወካዮች ምክር ቤት፣ ህውሃቶች እና ወይዘሮ አዜብ ካለምንም ሃፍረት አይናቸውን በጨው አጥበው የኢትዮጵያ ህዝብ የአቶ መለስ ራዕይ እንዲቀጥል ጠይቋል ይላሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ለአቶ መለስ የነበረውን ፍቅር ወይዘሮ አዜብ በጉባኤው ላይ ስትገልጽ፥ " ተሰብሳቢውን እስቲ እባካችሁ አንድ ጊዜ አይናችሁን ጨፍናችሁ የሃዘኑን ሰሞን አስታውሱ" ማለቷን ሪፖርተር ጋዜጣ ዘግቧል። የጉባኤው ተሰብሳቢ አይኑን በመጨፈን የኢትዮጵያን ህዝብ ሪፈረንደም ውጤት አስታወሰ ማለት ነው? መሳቂያ።

እንኳን የአገሩ መሪ አንድ ተራ ሰው እንኳን ሲሞት ህዘብ እስክስታ አይጨፍርም። ያዝናል። በሃዘን ሰሞን የተበደለውን ሁሉ ይቅር ይላል ህዝብ። ሞት ሲደርስ የእግዚአብሔር ጥሪ አድርጎ ያምናል አብዛኛው ህዝብ። ያዝናል። ነገ እሱም (ህዝብ) በተራ መንገደኛ መሆኑን ያስታውሳል። ያዝናል። ከልማድ፣ ከግብረገባዊ ትምህርቶቹ እና ከባህሉ የወረሳቸውን በማድረግ ሃዘኑን ይገልጻል ህዝብ ሰው ሲሞት። በቤት፣ በአደባባይ፣ እንደ ጥንቱ ከሆነ ደግሞ ቤተ መንግስት ቅጥር ግቢ ዙሪያ ተሰብስቦ ያዝናል ህዝብ መሪው ሲሞት። መሪውን በክብር ይቀብራል ህዝብ። ህዝብ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በንጹህ አዕምሮ እና በቀና መንፈስ እንጂ የራዕይ፣ የፖለቲካ፣ የስልጣን ጉዳይ ታውሰውት አይደለም። ሃዘኑ ፍጹም መንፈሳዊ ነው። ይኽን ማድረግ ግን የመለስ ራዕይ ይቀጥልልን የሚል ውሳኔ የያዘ ወረቀት በድምጽ መስጫ ሳጥኖች መከተት አይደለም።

በሃዘኑ ሰሞን የህውሃት ድራማም እንደነበር ማስታወስ ተገቢ ነው። ህዘቡ በተለያዩ የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ በስራ አጦች፣ በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በመምህራን፣ በሰራተኞች፣ በገበሬዎች እና ነጋዴዎች ማህበራት፣ በቤት ኪራይ፣ በእድር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በምሽት ጭፈራ ቤቶች የመንግስት 'የሃዘን ሰራዊት' መዋቅሮች አማካኝነት የሃዘን ልብስ ለብሶ (ለገሚሱም መንግስት ገዝቶ) ሃዘን እንዲደርስ መደረጉንም እናውቃለን። በዚህ አይነት መንገድ እንዲወጣ ቢደረግም ለአቶ መለስ ራዕይ ድምጽ ሰጠ ብሎ ማውራት ግን ዝቅተኛነት ነው። ከዚህ የምንማረው ነገር ቢኖር የዛሬዎቹ አምባገነኖች ለስልጣን ሲሉ የማይሉት እና የማያደርጉት ነገር እንደሌለ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በአቶ መለስ ራዕይ ላይ ያለውን አቅዋም ለመመዘን ምርጫ 97ን ማስታወስ ይጠቅማል።

(3ኛ) የኢትዮጵያ መንግስት፥
በስልጣን ላይ ያለ ገዢ ፓርቲ የሚገዛው (የሚያስተዳድረው) የሚደግፈውን ብቻ ሳይሆን የሚቃወመውንም ግብር ከፋይ ዜጎች ነው። መንግስታዊ ተቋሞች (የመንግስት መስሪያ ቤቶች) የገዢው ወይንም የተቃዋሚ ፓርቲ የግል መዋቅሮች አይደሉም። ስለዚህ በገዢ ፓርቲ እና በመንግስት (የመንግስት መስሪያ ቤቶች) መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት መኖር አለበት። የገዢው ፓርቲ መሪ ቢሞት እና ለሚቹ መታሰቢያ ተቋም መገንባት ቢያስፈልግ የፓርቲው እና የሚቹ ወዳጆች ጉዳይ እንጂ የመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ጉዳይ መደረግ የለበትም። አዋጁ ግን የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር፣ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የክልል ፕሬዘዳንቶች ሳይቀሩ በመታሰቢያ ተቋም ግንባታ እንዲሰማሩ ይደነግጋል። አዋጁ የፓርቲ መሪ መታሰቢያ ተቋም መገንቢያ ገንዘብ ምንጭ ደጋፊ ግብር ከፋዮች ብቻ ሳይሆኑ መላው የአገሪቱ ግብር ከፋዮች እንዲሆኑ ያስገድዳል። ለመታሰቢያ ተቋም የሚያስፈልጉ ነገሮች በሙሉ ከቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ ግሙሩክ እና የግሙሩክ ሰራተኞችን ያዛል አዋጁ።

በጉባኤው ላይ ከተሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ 72 ሚሊዮኑ ከደቡብ ኢትዮጵያ፣ ከአማራ፣ ከትግራይ፣ ከኦሮምያ፣ ከሶማሌ፣ ከአፋር፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ከሐረሪ፣ ከጋምቤላ የክልል መንግስቶች እና ከአዲስ አበባ አስተዳደር በመሆኑ የአቶ መለስን አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚቃወሙ ግብር ከፋዮች ሳይቀሩ ለመታሰቢያ ተቋሙ እንዲከፍሉ ተደርገዋል ማለት ነው። ዛሬ ባይሆንም ነገ በተለይ በህዝብ የተመረጠ መንግስት በኢትዮጵያ ሲመሰረት ግብር

ከፋዮች መታሰቢያ ተቋሙን ሊከሱ ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ ክስ የመመስረቿያ የጊዜ ገደብ (Statue of Limitation) ያለ አይመስለኝም። አያድርስ ነው እንጂ ወደፊት በአዜብ ላይ "የግብር ከፋይ ገንዘብ መልሺ" የሚል ሰላማዊ ሰልፍ ሊደረግ የሚችል ይመስለኛል። ለማንኛውም ከደጋፊዎች እና ከግሏ በምታገኘው ብቻ ብትገነባ ይሻላል። በአምባገነናዊ መዋቅር ከህዝብ የተዘረፈ ገንዘብ ባትጠቀም የሚሻል ይመስለኛል። ለአዜብ ነፃ ምክር።

(4ኛ) ሰለ አቶ መለስ መታሰቢያ ተቋም፥
የመታሰቢያ ተቋሙ ቤተ-መጽሐፍት፣ የምርምር ማዕከል፣ የስኮላርሽፕ፣ የህዝብ መዝናኛ (public park)፣ እና ሽልማት የሚሰጥ ክፍሎች እንደሚኖሩት ተዘግቧል። የአቶ መለስ እሬሳ የመጨረሻ ማረፊያ ቦታም እንደሚሆን ጠቅላይ ምኒስትር ኃይለማሪያም በጉባኤው ላይ መናገራቸውን ዋልታ ዜና ዘግቧል። የአቶ መለስ ቅርስ (Legacy) ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አዲሱ ለገሰ ለመታሰቢያ ተቋም መስራች ጉባኤ ባቀረበው ሪፖርት ላይ "የመለስ ዜናዊ መታሰቢያ ተቋም የሚገነባበት ሥፍራ ሰፋ ያለና ብዙ ነዋሪዎችን በማያፈናቅል ሁኔታ ሆኖ አመቺ ቦታ ተመርጧል" አመልክቷል። የሆነው ሆኖ አቶ አዲሱ ለገሰ ህዝብ አፈናቅሎ የሚገነባው መታሰቢያ ተቋም ከአርባጉጉ እና ከቤንሻንጉል-ጉምዝ የተሰማውን የተፈናቃይ ህዝብ ድምጽ ህያው ያደርጋል።

የመታሰቢያ ተቋሙ ግቦች የአቶ መለስን ራዕይ ከትውልድ ትውልድ ማሸጋገሪያ እና ማስረጫ እንደሚሆን ወ/ሮ አዜብ ደጋግማ ገልጻለች። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ካድሬዎች መቀፍቀፊያ መድረሳ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም ተቋሙ።

(5ኛ) ስለተመረጠው ቦርድ ጥቂት ልበል እና ይብቃኝ፥
በጉባኤው መጠናቀቂያ ላይ በወይዘሮ አዜብ ፕሬዘዳንትነት የሚመራ በጠቅላላ 13 ሰዎች ያሉበት ቦርድ የተመረጠ ሲሆን ሰዎቹም፥ (ሀ) ከመከላከያ ሚኒስቴር ጀነራል ሳሞራ የኑስ፣ (ለ) ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር አቶ ሶፊያን አህመድ፣ (ሐ) ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም፣ (መ) ከፌዴሬሽን ም/ቤት አቶ ካሳ ተ/ብርሃን፣ (ሠ) አዜብን ጨምሮ ከመለስ ቤተሰብ አራት ሰዎች፣ (ረ) ከአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች ደግሞ፣ (ረ-1) ከደቡብ ህዝቦች አቶ ሽፈራው ሽጉጤ፣ (ረ-2) ከአህዴድ ወ/ሮ አስቴር ማሞ፣ (ረ-3) ከህወሓት አቶ ቴዎድሮስ ሐጎስ፣ (ረ-4) ከሶማሌ ክልል አቶ አብዱ ዑመር መሐመድ (ረ-5) ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል አቶ አህመድ ናስር። ይህ ቦርድ የዛሬዎቹ አምባገነኖች ተጨማሪ የመንግስት ካቢኔ ይመስላል።

የሆነው ሆኖ የቦርዱ አባሎች በሙሉ ከአምባገነንነታቸው በስተቀር በዲሞክራሲ ባህላቸው፣ በነፃ አሳቢነታቸው፣ በኢትዮጵያ አንድነት እምነታቸው እና በዘመናዊ አስተሳሰብ ብቃታቸው የሚታወቁበት አንድም ማስረጃ የለም። ከአንድ እና ከሁለት ያህሉ በስተቀር አቶ መለስ ከጠመቃቸው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ውጭ ምንም ነገር የማያውቁ እና አዲስ የፖለቲካ አሳብ ማወቅ የማይፈልጉ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ይህ ቦርድ የሚመራው የመታሰቢያ ተቋም አቶ መለስ በህይወት ሳለ ያራመዳቸውን ፀረ-ነፃነት፣ ፀረ-ዲሞክራሲ፣ ጸረ-ነፃ ምርጫ፣ ህግ በፖለቲካ የሚገዛበትን፣ ፍትህ-አልባ እና ህዝብ አፈናቃይ ፖሊሲዎች የሚያስቀጥል ተቋም እንደሚሆን መገመት ይቻላል። አሳፋሪ ተቋም።

የመጀመሪያ ልጃቸው (ስምሃል መለስ) መንግስት መታሰቢያ ተቋሙን ተቆጣጠረው በማለት በቦርዱ ላይ ያላትን ቅሬታ በጉባኤው ላይ በይፋ ለተሰብሳቢው መግለጿ ተዘግቧል። ስምሃል የተሰማትን በነፃ በመናገሯ በነፃ የማሰብ እና የመናገር መብት በመገድ የሰለጠኑት ሶስት አምባገነኖች (አቶ አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ስምኦን እና እናቷ አዜብ) በልጅቷ ላይ ተረባረቡባት። ስለ ስምሃል ከተዘገበው በስተቀር ምንም አላውቅም። ከተዘገበው ግን በዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤትነት ስምሃል ሶስቱንም አምባገነኖች እንደምትበልጥ መገመት አያዳግትም። ስምሃል አባትዋን ልትደግፍ ትችላለች። መብቷ ነው። በወላጆቿ የተፈጸመው ስህተት እሷን አይመለከትም።

መደምደሚያ። የሆነው ሁሉ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ግን ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ዛሬም የማፈናቀል ባለቤት ህዝብ አይደለም። ዛሬም እንደትናንቱ ህዝብን የማፈናቀል ባለቤት ለማድረግ ፖለቲከኞች ያደረጉዋቸው ሙከራዎች ከሽፈዋል። ለመለስ ራዕይ መታሰቢያ ተቋም ለመገንባት ኅንበስ ቀና ከሚሉት ውስጥም ቢሆን ከተወሰኑት በስተቀር አብዛኛው የህውሃት አባል ራዕዩን የሚደግፍበት ምክንያት አቶ መለስ ያካባቢ ተወላጅ እና የጎሳ ዘመዳቸው በመሆኑ እንጂ በኢትዮጵያ ላይ የደቀኑብንን አደጋ ተገንዝበው እና አቶ መለስ በልጠባቸው አይመስለኝም። ስለዚኽ አገር ወዳድ የሆን በጽሑፍ፣ በዜና ማሰራጫዎች እና በአፍ (በስልክ)አማካኝነት ሁሉ የአቶ መለስ ራዕይ ለኢትዮጵያ ጎጂ መሆኑን የማሳወቅ ሰፊ ዘመቻ በህውሃት/ኢህአዴግ አባላት ላይ ማድረግ አለበን።